**ለSeattle’s Environmental Justice Fund (የሲያትል የአካባቢ ፍትህ ፈንድ) ያመልክቱ**

የSeattleን የአየር ንብረት ግቦች ለማሳካት የእያንዳንዱ ሰው ተሳትፎ ያስፈልጋል። በመሆኑም Seattle’s Office of Sustainability & Environment (OSE፣ የሲያትል የዘላቂነት እና የአካባቢ ጥበቃ ቢሮ) የ2026 ዓ.ም Environmental Justice (EJ) Fund (የአካባቢ ፍትህ ፈንድ) ማመልከቻ **አሁን ክፍት መሆኑን በደስታ ያሳውቃል!** እንደ Environmental Justice Fund ያሉ ኢንቨስትመንቶች፣ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎችን የሚያፋጥኑ መሰረታዊ እና በማህበረሰብ-የሚመሩ መፍትሄዎችን ለመደገፍ የተቀረጹ የሲያትል ስትራቴጂ አካል ናቸው።

EJ Fund ድጋፍ የሚያደርገው ከሚከተሉት አራት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ከአንዱ ጋር ለሚጣጣሙ ፕሮጀክቶች ነው፡- 1) በአየር ንብረት ለውጥ ቀድመውና በከፋ ሁኔታ ለተጎዱ ማህበረሰቦች የአመራር ብቃትን መገንባት፣ 2) በማህበረሰብ የሚመሩ የአየር ንብረት ወይም የአካባቢ መፍትሄዎችን መደገፍ፣ 3) ከአየር ንብረት ጋር ለተያያዙ የስራ መስኮች ስልጠናዎችን እና ግንዛቤዎችን መስጠት እና 4) ጤናን እና የማህበረሰብ ደህንነትን ለመጠበቅ የመቋቋም አቅምን መገንባት።

EJ Fund በጥቁሮች፣ በሀገሩ ተወላጆች እና የተለያየ ቀለም ባላቸው ማህበረሰቦች (BIPOC)፣ በስደተኞች፣ በሌላ ሀገር ዜጎች፣ በወጣቶች፣ በዕድሜ ባለጸጎች እና አነስተኛ ገቢ ባላቸው ነዋሪዎች በሚመሩ ወይም ከእነሱ ጋር አጋርነት በፈጠሩ ፕሮጀክቶች ላይ ኢንቨስት ያደርጋል። ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ሰፈሮች ለሚያገለግሉ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ ይሰጣል፡- Beacon Hill፣ Bitter Lake፣ Central Area፣ Chinatown-International District፣ Delridge፣ Georgetown፣ Haller Lake፣ Lake City፣ Mount Baker፣ Othello፣ Rainier Beach እና South Park።

ጎሳዎችና የጎሳ ድርጅቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች እንዲሁም የማህበረሰብ እና የሰፈር ቡድኖች ለዚህ የገንዘብ ድጋፍ (ፈንድ) ብቁ ናቸው። ብቁ የሆኑ ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እና ለማጣጣም (ለመለማመድ) የሚረዱ መፍትሄዎች
- የማህበረሰብ ዕቅድ እና የጋራ ራዕይ ቀረጻ
- ባህላዊ እውቀቶችን ጠብቆ ማቆየት እና/ወይም ማስተማር
- በአካባቢ ጥበቃ ወይም በአየር ንብረት ዙሪያ የሚሰሩ የስነ-ጥበብ እና የትረካ ስራዎች
- የአካባቢ ጥበቃ ወይም የአየር ንብረት ግንዛቤ ማስጨበጫ፣ የማህበረሰብ ተደራሽነት እና/ወይም የጋራ ተሳትፎ ስራዎች
- ከአየር ንብረት ጋር በተያያዙ የሙያ መስኮች ላይ ዕውቀትና ተሞክሮ የሚያስጨብጡ ፕሮግራሞች
- የድርጅት እና የማህበረሰብ አቅም ግንባታ

በዚህ ዓመት፣ፕሮጀክቶች በ22 ወራት ውስጥ ሊከናወኑ የሚችሉ ሲሆን፣ የግድ ፌብሩዋሪ 2027 ተጀምረው ኖቬምበር 2028 መጠናቀቅ አለባቸው። **ሁለት ዓይነት የገንዘብ ድጋፍ አማራጮች** አሉ፡-

- አማራጭ 1፡- ከ$60,000 እስከ $80,000 የሚደርስ የገንዘብ ድጋፍ
- አማራጭ 2፡- ከ$80,001 እስከ $120,000 የሚደርስ የገንዘብ ድጋፍ

## እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

አንደኛ፡- እስከ ጁላይ 14 ቀን 5 ሰዓት ፒ.ኤም ድረስ ለማመልከት ብቁ መሆንዎን ያረጋግጡ

- **ማሳሰቢያ፡-** ይህ ሙሉ ማመልከቻዎን ለማስገባት የተቀመጠ **ቅድመ ሁኔታ** ነው።
- ይህንን ተግባር እንዳጠናቀቁ፣ *ቀደም ሲል የገንዘብ ድጋፍ ጠይቀው የማያውቁ ከሆነ* ማመልከቻዎን ለማሟላት የሚረዳዎት አማካሪ ይመደብልዎታል።

ሁለተኛ፡- የተሟላ ማመልከቻዎን ያስገቡ

**ከእኛ ጋር ይገናኙ!**
ስለ ፈንዱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ በፕሮጀክት ዕቅድ ላይ ለመወያየት ወይም ማመልከቻ ለማቅረብ ከፈለጉ፣ከሚከተሉት መንገዶች አንዱን እንዲከተሉ እናበረታታዎታለን፡-

1. በቨርቹዋል የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃግብር ላይ ይሳተፉ፡-
    a. ረቡዕ፣ ጁን 10 ቀን 2026 ከ6 - 7:15 ሰዓት ፒ.ኤም።
        i. እዚህ ይመዝገቡ
    b. ማክሰኞ፣ ጁን 30 ቀን 2026 ከ12 እስከ 1:15 ሰዓት ፒ.ኤም።
        i. እዚህ ይመዝገቡ

2. ከEJ Fund ሰራተኞች ጋር በቨርቹዋል የቢሮ ሰዓታት ላይ ይሳተፉ፡-
    a. ረቡዕ፣ ጁን 17 ቀን ከ12-1 ሰዓት ፒ.ኤም
        i. በZoom (ዙም) ስብሰባውን ይቀላቀሉ
    b. ረቡዕ፣ ጁላይ 8 ቀን ከ12-1 ሰዓት ፒ.ኤም
        i. በZoom (ዙም) ስብሰባውን ይቀላቀሉ

3. ማንኛውንም ጥያቄ በequityenviro@seattle.gov ኢሜይል ያድርጉልን

ለማብራሪያ (ግንዛቤ ማስጨበጫ) መድረኮች ወይም ለቢሮ ሰዓታት አስተርጓሚ እንዲመደብልዎ ወይም ሁኔታዎች እንዲመቻችልዎ ለመጠየቅ፣ እባክዎን ለመሳተፍ ካሰቡበት መርሃ-ግብር ቢያንስ 3 የስራ ቀናት ቀደም ብለው ወደ equityenviro@seattle.gov ኢሜይል ያድርጉ።